የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.5
ADDIS ABABA, 26th December, 2014

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፫፻፳፯/፪ሺ፯ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ....ገጽ ፯ሺ፰፻፵፰

**CONTENTS**

Regulation No. 327/2014

Ethiopian Environment and Forest Research Institute Establishment Council of Ministers Regulation ....Page 7848

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፯/፪ሺ፯

## የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

በሀገራችን የሚካሄዱት የልማት ስራዎች ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃ የደን ልማት አያያዝና አጠቃቀምን የሚያረጋግጡ በማድረግ የታቀደውን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስትራተጂ ግብን ለማሳካትና ሀገራችን ከተፈጥሮ ሀብቶቿ ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ ማስቻል በማስፈለጉ፤

ለአካባቢና ለደን ምርምር ሥራዎች ትኩረት በመስጠት የሀገሪቱን ከፍተኛ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ ሁኔታ በተቀናጀና በአንድ ወጥ የምርምር ሥርዓት ውስጥ ማደራጀት በማስፈለጉ፤

መንግሥት ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ሥራዎች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የአካባቢና ደን ሚኒስቴርን ያቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የደን ምርምርን ከአባባቢ ጥበቃ ምርምር ጋር በኢንስቲትዩት ደረጃ ማስተሳሰር በማስፈለጉ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ (በአዋጅ ቁጥር ፰፻፫/፪ሺ፭ እንደተሻሻለው) አንቀጽ ፭ እና ፴፭ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 327/2014

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN ENVIRONMENT AND FOREST RESEARCH INSTITUTE

WHEREAS, it is found necessary to make the development activities underway in the country ensure environmental protection and sustainable forest management and use, to succeed the green development strategy for the planned climate change mitigation and to enable the country to get appropriate benefit from its natural resources;

WHEREAS, it is found necessary to make the research activities to be undertaken in an integrated and consistent system that ensures the highest benefit to the country by giving special attention to environment and forest research activities;

WHEREAS, it is found necessary to give due attention to activities of environmental protection and, forest development, protection and utilization activities by linking forest research with environmental protection research at an institutional level for the attainment of the objectives of the Government which initiated establishment of the Ministry of Environment and Forest;

NOW THEREFORE, this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 35 of the Definition of Power and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 (as amended by Proclamation No. 803/2013).

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፯/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "የአካባቢና የደን ምርምር" ማለት በደንና ጥምር እርሻ ደን ልማት፣ አያያዝ፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀም እና የአካባቢ ጥበቃ ላይ ምርምር ማካሔድ፣ ቴክኖሎጂዎችን፣ መረጃዎችና ዕውቀቶችን ማውጣት፣ ማሰራጨት እና ማስተዋወቅ ነው፤

፪/ "ሥነ-ምህዳር" ማለት በአንድ በተወሰነ አካባቢ ውስጥ የዕጽዋት፣ እንስሳት እና ደቂቀ አካላት ስብስብ ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች ጋር በመስተጋብር ያለማቋረጥ በዝግመተ ለውጥ ውስጥ የሚኖሩበት ሥርዓት ነው፤

፫/ "አካባቢ" እና "ብክለት" የሚሉት ቃላት እንደየቅደም ተከተላቸው በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ፫፻/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፪ (፮) እና (፲፪) የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤

፬/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደርንም ይጨምራል፤

፭/ "ማዕከል" ማለት የአካባቢና የደን ምርምር ሥራዎችን የሚያካሂድ የአካባቢና ደን ምርምር ኢንስቲትዩቱ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ነው፤

፮/ "ሚኒስቴር" ማለት የአካባቢና የደን ሚኒስቴር ነው፤

፯/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፰/ በወንድ ፆታ የተገለፀው ማንኛውም አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Environment and Forest Research Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 327/2014".

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "environment and forest research" means conducting research on forestry and agro-forestry development, management, conservation and utilization and environmental conservation and thereby generate and disseminate technologies, information and knowledge;

2/ "ecology" means a system in which plants, animals and micro organisms, which are known as living things, are living in continuous evolutionary interaction with non-living things in a specific place;

3/ "environment" and "pollution" shall have the meanings assigned to them under Article 2 (6) and (12) of the Environmental Pollution Control Proclamation No. 300/2002, respectively;

4/ "Region" means any state referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

5/ "center" means a branch office of Environment and Forest Research Institute that conducts research activities on environment and forest;

6/ "Ministry" means the Ministry of Environment and Forest;

7/ "person" means any natural or legal person;

8/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

**፫. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት") እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፭. ዓላማ**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ በሀገራችን የተኩረት አቅጣጫዎች እና የተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ያተኮሩ ለደን ልማት፣ የአካባቢ ጥበቃ ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ቴክኖሎጂዎችን መለየት፣ ማስገባት፣ ማላመድ፣ ጥቅም ላይ ማዋል እና ማፍለቅ፤

፪/ በአካባቢና ደን ምርምር ማዕከላት ወይም በውል አማካይነት የአካባቢና ደን ምርምር በሚያከናውኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ሌሎች መሰል ተቋማት የሚካሄዱትን የአካባቢና ደን ምርምር ተግባራትን ማስተባበር፤

፫/ የአካባቢና የደን ምርምርን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና በልማት ፍላጎት ላይ ያተኮረ ለማድረግ የሚያስችል አቅም መገንባት እና ሥርዓት መዘርጋት፤

፬/ የአካባቢና የደን ምርምር ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማስተዋወቅ፡፡

**፮. ሥልጣንና ተግባራት**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የሀገሪቱን የልማትና የምርምር ፖሊሲዎች መሰረት በማድረግ የአካባቢና የደን ጥበቃ ምርምር ስትራቴጂ የመንደፍ፣ የስራ ፕሮግራምና እቅድ የማዘጋጀት፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ የማድረግ እንዲሁም በሚመለከታቸው ክፍሎች ተግባራዊ መሆኑን የመከታተል፤

**3. Establishment**

1/ The Ethiopian Environment and Forest Research Institute (herein after referred to as the Institute) is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

**4. Head Office**

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

**5. Objective**

The Institute shall have the following main objectives:

1/ identify, import, adapt, utilize and generate technologies that significantly contribute to forest development and environmental protection that focuses on the priorities of the country and demand of users;

2/ coordinate the environment and forest research activities carried out by environment and forest research centers or higher education institutes and other related facilities conduct research on the basis of contract;

3/ build capacity and establish a system that enables the environment and forest research activities to be efficient, effective and development-based;

4/ disseminate the environment and forest research outputs to users.

**6. Powers and Duties**

The Institute shall have the following powers and duties:

1/ design environment and forest conservation research strategy based on the development and research policies of the country; prepare action plans and schedules, and implement same upon approval as well as follow up the implementation thereof by the concerned organs;

፪/ ከአገሪቱ የልማት አቅጣጫ እና ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ የአካባቢና የደን ምርምር ፕሮጀክቶች ለመቅረጽ የሚያስችል መመሪያ የማዘጋጀት፣ እንደ አግባቡ ተዘጋጅ ተው የሚቀርቡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በጀታቸውን በመገምገም በመመሪያው መሠረት መዘጋጀታቸውን የማረጋገጥ እና ለመንግሥት አቅርቦ የማስጸደቅ፤

፫/ መንግሥት በሚፈቅደው በጀት መሠረት የአካ ባቢና የደን ምርምር ማዕከላትን፣ ላቦራቶሪ ዎችን እና ጣቢያዎችን የማደራጀት፣ አዳዲስ ማዕከላትንና ጣቢያዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በተለያዩ ክልሎች እና ስነምህዳሮች እንዲቋ ቋሙ የማድረግ ወይም የተቋቋሙት እንዲታ ጠፉም የማድረግ፤

፬/ ጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ የአካባቢና የደን ምርምር ውጤቶችን ተጠቃሚው እንዲያ ውቃቸው ለማድረግ አግባብ ካላቸው ኤክስቴንሽን አካላት ጋር በመተባበር የአህዝቦት ተግባር የማከናወን፤

፭/ በሀገሪቱ ጎልቶ የሚታየውን የአካባቢ መራቆት፣ የበረሃማነት መስፋፋት እንዲሁም የዝርያዎች መጥፋትን ለመቀነስና የደን ውጤቶች የአቅር ቦት ችግርን ለመፍታት የሚያስችሉ ፈጣን እድገት ያላቸውን የዕፅዋት ዝርያዎችን የማላ መድ እና የማሰራጨት፤

፮/ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስ ቃሴዎች ምክንያት በአካባቢ ላይ የሚደር ሰውን የሚዛን መዛባት፣ ብክለትን እና ተዛማጅ ችግሮችን በመለየት የሚቀንሱበትን እና መልሰዉ የሚያገግሙበትን መንገድ የማመቻቸት፤

፯/ በሀገር ውስጥና በውጭ አገራት የተካሄዱና የሚካሄዱ ለአካባቢና ደን ምርምር የሚጠ ቅሙ ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማከ ማቸት እና የማሰራጨት፤ የመረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓትን የመገንባት እና የማስተባበር፤

፰/ ለክልል የግብርና፣ የአካባቢና የደን ምርምር ማዕከላት እና ለሌሎች ተገልጋዮች ተገቢውን የመረጃ አገልግሎት የመስጠት፤ ጥያቄም ሲቀርብ አቅም በፈቀደ መሰረት የቴክኒክ ድጋፍ የማድረግ፤

2/ issue directive that enable the designing of environment and forest research programs and projects that will be in line with the development direction of the country and the need of the users; evaluates budget of programs and projects and ensures that they are prepared as per the directive and submits same to the Government for approval;

3/ organize environment and forest research centers, laboratories and stations; as may be necessary, establish new centers and stations in different regional states and ecological areas based on the budget allocated by the Government, or may close down centers and stations established;

4/ undertake the necessary public mobilization activities in cooperation with the relevant extension organs to disseminate validated environment and forest research findings to the users;

5/ adapt and distribute fast growing tree species that enable to mitigate environmental degradation, desertification, and extinction of species and solve problem of forest products supply;

6/ identify the imbalance, pollutions and other related problems inflicted on environment due to socioeconomic activities and facilitates alleviation of the problems and rehabilitation paths;

7/ collect, store and disseminate research outputs produced and to be produced at local and international level which are useful for forest and environment research works; establish and coordinate information networks and distribution systems;

8/ provide proper information service to regional agriculture, environment and forest research centers and other service seekers, and provide technical support as per the available capacity, when requested;

፱/ በኢንስቲትዩቱ እና በሌሎች አካላት በሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽና የሀብት ብክነት እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክቶች ክትትል እና ግምገማ ሥርዓት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የመዘርጋት እና አፈፃፀሙንም የመከታተል፤

፲/ ከዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ፣ አካባቢ እና ሀገራዊ የየደን ምርምር ተቋማት እና ደጋፊ ድርጅቶች እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው አካላት ጋር ግንኙነት መመሥረትና ትብብር የማድረግ፤

፲፩/ በአካባቢና የደን ምርምር ላይ የተሰማራን ማንኛውም ሰው መዝግቦ ዝርዝሩን የመያዝ፤

፲፪/ በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት ከአገልግሎት ተቀባዮች የአገልግሎት ክፍያ የመሰብሰብ፤

፲፫/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

፲፬/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

**፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>**

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፪/ አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

**፰. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲዩቱን የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሰረት፣ እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈፀም ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች መንግስት ለግብርና

9/ establish necessary project monitoring and evaluation system in consultation with the concerned organs in order to avoid unnecessary redundancy and wastage of resources for conducting research and follows up its implementation;

10/ establish relationships and cooperate with international, continental, regional and local environment and forest research institutes, donor organizations and with other bodies having similar objectives;

11/ register and keep record of any person who is engaged in environment and forest research;

12/ charge fees for the services it renders in accordance with the rate approved by the Government;

13/ own property, enter into contract and sue and be sued in its own name;

14/ perform such other activities as are conducive to the attainment of its objectives.

**7. <u>Organization of the Institute</u>**

The Institute shall have:

1/ a Director General and, as may be necessary, Deputy Director Generals to be appointed by the Government; and

2/ the necessary staff.

**8. <u>Powers and Duties of the Director General</u>**

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall, subject to the general direction of the Ministry, direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without limiting the generality sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the power and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Institute in accordance with the federal civil service laws and, in the case of professionals engaged in the core functions of the Institute, in accordance with the directive

ተመራማሪዎች ባጸደቀው መመሪያ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ) የኢንስቲትዩትን ስትራተጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፱. በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

**፲. የሒሳብ መዛግብት**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**፲፩. የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፸፱/፲፱፻፹፱ (በአዋጅ ቁጥር ፫፻፹፪/፲፱፻፺፮ እንደተሻሻለው) አንቀጽ ፲፯ መሠረት ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ድርጅት የተላለፉ የደን ምርምር እና የደን ዉጤቶች አጠቃቀም ምርምር ተቋማት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል፡፡

approved by the Government for agricultural researchers;

c) prepare and submit to the Ministry the strategic plan, annual plan, work program and budget of the Institute and implement the same up on approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

**9. Budget**

The Institute's budget shall be allocated by the Government.

**10. Books of Accounts**

1/ The Institute shall keep complete and accurate book of accounts.

2/ The book of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or an Auditor designated by him.

**11. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and duties transferred to the Ethiopian Agricultural Research Organization under Article 17 of the Ethiopian Agricultural Research Organization Establishment Proclamation No. 79/1997 (as amended by Proclamation No. 382/2004) with respect to forestry research and wood utilization research are hereby transferred to the Institute.

፲፪. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

12. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 26th day of December 2014.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት